**ደህንነት** ማለት *ከሚመጣው ፍርድ መዳን ብቻ ሳይሆን በሕይወት ሳሉ ከኃጥያት ኃይል መዳን ማለት ነው፤* (አንድ ሰው ከዳነ በኋላ፡- **ከኃጥያት ይለያል፡-** የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑት ስጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ፡፡ገላ 5፡24)፣ **(አዲስ ፍጥረት ይሆናል**፡- ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል፡፡2ቆሮ 5፡17)፣ **(ይቀደሳል፡-** በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፣ ተቀድሳችኋል፣ ጸድቃችኋል.1ቆሮ 6፡11)፡፡

## ሰው የዳነው እንዴት ነው?

*ሰው ሁሉ የዳነው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው፡፡ ጸጋ ማለት ለማይገባው ማንነት እንዲሁ የሚሰጥ ነጻ ስጦታ ነው (ሮሜ 3፡23)።* በመሆኑም እጅግ ንጹህና ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር እጅግ በጣም ኃጥያተኛ ከሆነው ሰው ጋር የሚገናኘው በጸጋ አማካኝነት ብቻ ነው፡፡

ጸጋ በሰው ልፋትና የጽድቅ ስራ የሚገኝ ሳይሆን እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሰራውን የተጠናቀቀ የደህንነት ስራ በማመን ብቻ የራሳችን የምናደርገው ለኃጢያተኞች የተዘጋጀ የደህንነት መንገድ ነው (ሮሜ 4፡4. ለሚሰራ ደመወዝ.....)

ጸጋ በዓለም ላይ ከሚፈጸመው ኃጥያት በሙሉ ከመጠን ይልቅ የሚበልጥና በእምነት ለሚቀበሉት ሁሉ ደህንነትን (የዘላለም ሕይወትን) የሚሰጥ የእግዚአብሔር የማዳን አሰራር ነው፡፡ (ሮሜ 5፡15-21)

ጸጋ እኛ በጎ ወይም ክፉ በማድረጋችን የምናገኘው ወይም የምናመጣው ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኛችን አድርገን በእምነት በመቀበል ብቻ የምናገኘው በመሆኑ በስራ እንደጸደቀ ሰው ፈጽሞ በራሳችን ልንመካ አንችልም፡፡ (ሮሜ 9፡10-18 ነገርግን ርብቃ ደግሞ…)፣ (ኤፌ 2፡8 ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም.. ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም)

- **ዮሐ 1፡17** ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ
- **ቲቶ 2፡11** ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጧልና
- **ኤፌ 2፡4.** በበደላችሁ እና በኃጥያታችሁ ሙታን ነበራችሁ….(4)ነገር ግን እግዚአብሔር በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ በበደላችን ሙታን እንኳን በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን. በጸጋ ድናችኋልና፡፡
- **ቲቶ 3፡4**. ነገርግን የመድሐኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ስራ አይደለም፡፡ ያን መንፈስም በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድሐኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው፡፡ ቃሉ የታመነ ነው፡፡
- **ዮሐ 3፡16.** በእርሱ የሚያምን የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጅ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር….
- **1ዮሐ 4፡9.** በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር ከእኛ ዘንድ ተገለጠ. በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ አለም ልኮታልና፡፡ ፍቅርም እንደዚህ ነው እግዚአብሔር እርሱ እራሱ እንደወደደን ስለ ኃጥያታችንም ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም፡፡
- **ሮሜ 5፡10**. ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፡፡

**የፀጋው አሰራር**

- እግዚአብሔር ቃል ስጋ ሆነ፤ ዮሐ 1፡14
- እግዚአብሔር ቃሉን (ልጁን) የዓለም መድሐኒት ሊሆን ላከው. 1ዮሐ 4፡14 እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዐለም መድሐኒት ሊሆን እንደላከው እንመሰክራለን፡፡
- እግዚአብሔር ልጁን በእኛ ምትክ እንዲሞት እኛ ደግሞ በእርሱ ጽድቅ እንዲሁ እንድንጸድቅ አደረገ 2ቆሮ 5፡21- እኛ በእርሱ …ገላ 3፡13 ከእርግማን ዋጀን

## ለመዳን ጌታ ኢየሱስን ብቻ ለምን መረጥን?

ምክንያቱም:

እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ሮሜ 10፡17

- እርሱ ብቻ አዳኝ ስለሆነ. **ኢሳ 43፡11**. እኔ ÷ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም **ሐዋ 4፡12**. መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና.
- ለኃጢያታችን የሞተው እርሱ ብቻ ስለሆነ. **ዮሐ 3፡15**. ሙሴ በምድረበዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል፡፡ **1ቆሮ 15፡3**. መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ሐጥያታችን ሞተ ተቀበረም መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛ ቀን ተነሳ. **1ጴጥ 2፡24**. ለኃጥያት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጥያታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ. **ሮሜ 5፡8**. ነገር ግን ገና ኃጥያተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል፡፡
- ከኃጥያት የሚያነጻው የእርሱ ደም ብቻ ስለሆነ. **1ዮሐ 1፡7** የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጥያት ሁሉ ያነጻናል
- በእርሱ ብቻ ወደ አብ ስለሚደረስ፡ **ዮሐ 14፡6**. እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም. **ኤፌ 2፡18.** በእርሱ ስራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና፡፡
- ሕይወት እርሱ ብቻ ስለሆነ. **ዮሐ 14፡6**. እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ
- በእርሱ የሚያምን የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጅ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና **ዮሐ 3፡16.**
- የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና፡፡ **ሮሜ 10፡13**
- ...ጌቶች ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል አላቸው፡፡ እነርሱም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት፡፡ **ሐዋ 16፡30-31**

## ሰው የሚጸድቀው ጸጋውን በእምነት በመቀበል ብቻ ነው፡፡

1. እስራኤል (ሐዋርያትን ጨምሮ) የዳኑት በጸጋ ብቻ ነው **(ሐዋ 15፡11**. ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደ እነርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ እናምናለን፡፡)
2. የእግዚአብሔር ጽድቅ የሚገኘው የኢየሱስን ቤዛነት በማመን በጸጋ ብቻ ነው **(ሮሜ 3፡21**. አሁን ግን በህግና በነቢያት... እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ **በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው**)
3. በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል **እንዲያው በጸጋው** ጸድቀናል **(ሮሜ 3፡24)**
4. ሰው ያለ ሕግ ስራ በእምነት ይጸድቃል (ሮሜ 3፡27-29 ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው; ...ሰው ያለ ሕግ ስራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና)
5. የዳንነው በጸጋ እንጂ እግዚአብሔር ግዴታ (ዕዳ) ስላለበት አይደለም (ሮሜ 4፡4)
6. እግዚአብሔር ያለ ስራ (በጸጋ) ጽድቅን ቆጥሮልናል (ሮሜ 4፡5)
7. ያለ ስራ ጽድቅ የሚቆጠርለት ሰው ብጹዕ ነው (ሮሜ 4፡6)
8. ስራ በጸጋ የመጽደቃችን ማህተም እንጂ የመጽደቂያ መንገድ አይደለም (ሮሜ 4፡9-12. ቁ.11 ሳይገረዝ በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማህተም የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ)
9. እምነታችን ጽድቅ ሆኖ የሚቆጠረው **ከመስራታችን አስቀድሞ ነው** (ሮሜ 4፡11)
10. እምነት ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረው ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን ለእኛም ነው (ሮሜ 4፡23-25. ነገርግን ተቆጠረለት የሚለው.....ቁ.24 ስለ በደላችን አልፎ ተሰጠውን እኛን ስለማጽደቅም ተነሳውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሳው ለምናምን ለእኛ ይቆጠርልን ዘንድ አለው፡፡)
11. በእምነት ስለጸደቅን ሰላም ሊኖረን ይገባል (ሮሜ 5፡1)
12. እግዚአብሔር ጸጋውን የላከው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስለሆነ በአዳም ከመጣብን ኃጥያት ይልቅ ጸጋው እኛን ለማጽደቅ እጅግ ብልጫ አለው (ሮሜ 5፡12-21)
13. የምንጸድቀው በአንድ ሰው (በኢየሱስ) መታዘዝ ነው ( ሮሜ 5፤18-21)
14. አማኝ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደለምና ኃጥያት አይገዛውም (ሮሜ 6፡14፣ ቲቶ 2፡11)

እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ሮሜ 10፡17

15. በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ኩነኔ ፈጽሞ የለባቸውም (ሮሜ 8፡1)
16. ከኃጥያትና ከሞት ህግ አርነት ወጥተናል (ሮሜ 8፡2)
17. የሚያጸድቀን እራሱ እግዚአብሔር ነው (ሮሜ 8፡30. የልጁን መልክ እንዲመስሉ ወሰናቸውን ጠራቸው ጠራቸውንም አጸደቃቸው. 8፡34. የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኮንንስ ማነው)
18. ጽድቅ ከጠሪው እንጂ ከስራ አይደለም (ሮሜ 9፡10-13)
19. ምህረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም (ሮሜ 9፡14-18)
20. በእምነት ጽድቅን ማግኘት ሲቻል በሥራ ግን ፈጽሞ አይቻልም (ሮሜ 9፡30 ጽድቅን ያልተከተሉት አህዛብ ጽድቅን አገኙ እርሱ ግን ከእምነት የሆነ ጽድቅ ነው)
21. የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የህግ ፍጻሜ ነው (ሮሜ 10፡3-4)
22. ደህንነት የሚገኘው በልብና በአፍ ላይ በተዘጋጀው በእምነት ቃል እንጂ ህግን በማድረግ አይደለም፡፡( ሮሜ 10፡8-10 ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን.)
23. ከእስራኤልም የሚመረጡት በጸጋ እንጂ በሥራ አይደለም (ሮሜ 11፡5. እንደዚሁም በአሁኑ ዘመን ደግሞ በጸጋ ተመረጡ ቅሬታዎች አሉ፡፡ በጸጋ ከሆነ ግን ከሥራ መሆኑ ቀርቶአል፤ ጸጋ ያለዚያ ጸጋ መሆኑ ቀርቶአል)
24. እስራኤል የተቆረጡት ባለማመናቸው ነው (ሮሜ 11፡20.)
25. የተጠራነው በክርስቶስ የጸጋ ወንጌል ነው (ገላ 1፡6)
26. ከጸጋ ወንጌል ውጭ የሚሰብክ ማንኛውም ፍጥረት በመለኮታዊ እርግማን ስር ነው (ገላ 1፡6-9)
27. በጸጋ ከዳንን የሕግ ሰባኪዎች አርነታችንን (ነጻነታችንን) እንዲሰልሉ ልንፈቅድላቸው ፈጽሞ አይገባም (ገላ 2፡3-5)
28. የወንጌል እውነት ጸንቶ እንዲኖር ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች እንኳን ወደ ሕግ ፈቀቅ ቢሉ ሊወቀሱ ይገባቸዋል (ገላ 2፡11-21)
29. **ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ ሕግን በመፈጸም ከቶ ሊጸድቅ አይችልም፡፡** (ገላ 2፡16 ነገርግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ስራ እንዳይሆን አውቀን ስጋን የለበሰ ሁሉ በህግ ስራ ስለማይጸድቅ እኛ ራሳችን በህግ ስራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል)
30. የእግዚአብሔርን ጸጋ መጣል አይገባም (ገላ 2፡21)
31. ጽድቅ የሚገኘው ሕግን በመፈጸም ከሆነ ክርስቶስ መሞት አያስፈልገውም ነበር(ገላ 5፡21)
32. መንፈስ ቅዱስን የተቀበልነው፤ ምልክቶችና ተአምራት የሚደረጉት ቃሉን በእምነት በመስማታችን እንጂ ህጉን በመጠበቃችን አይደለም (ገላ 3፡1-5)
33. በእምነት የጸደቁ በሙሉ የአብርሃም ልጆች ናቸው (ገላ 3፡6-9)
34. ጻድቅ በእምነት ይኖራል እንጂ በሥራው አይመካም (ገላ 3፡11)
35. የተስፋው ቃል ለሚያምኑ ብቻ ይሰጣል ( ገላ 3፡21-22)
36. የህግ ሰባኪዎችና ትምህርቱን የተቀበሉ ወደ ውጭ ሲጣሉ የተስፋው ቃል ልጆች ግን ይወርሳሉ (ገላ 4፡21-31)
37. ከህግ ት/ት ነጻነት ወጥተናል ( ገላ 5፡1)
38. ከስራ ሳይሆን ከእምነት ጽድቅን ተስፋ እንጠባበቃለን (ገላ 5፡5)
39. ከዚህ እውነት የሚያናውጡን ፍርዱን ይሸከማሉ (ሐዋ 15፡24፣ ገላ 5፡9-11)
40. የተመረጥነው ስለ መልካም ስራችን ሳይሆን ገና ዓለም ሳፈጠር በፊት ነበር፡፡ ስለዚህ ጸጋው እንዲያው ተሰጠን ነው እንጂ በጽድቃችን ያገኘነው አይደለም (ኤፌ1፡4-6፣ 2፡1-5)
41. ጸጋው በእምነት ብቻ አድኖናልና በሥራችን አንመካም ( ኤፌ 2፡8-10)
42. እኛ በአደረግነው ሥራ ሳይሆን በጸጋው ጸድቀናል (ቲቶ 3፡3-7)
43. ይህ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ካልሆነ ጥፋት ይሆናል (ሐዋ 13፡38-43)

## በሥራ የሚገለጠው እውነተኛ እምነት

**መልካም ስራ** ለእግዚአብሔር ህግ መታዘዝ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸምና የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት ነው፡፡ይህም የእግዚአብሔር ሰው ያሰኛል፡፡ ማቴ 5፡16፣ ዮሐ 4፡34፣ 6፡28-29፣ 8፡39፣ 10፡32፣ 14፡12፡፡ ሰው ያለ እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት አይችልም ዕብ 11፡6፡፡ ይልቁንም ሰው በክርስቶስ ሲያምን የተለወጠ ልብ ስለሚኖረው መልካም ሥራ ይሰራል ለዚህም ሥራ

**ይመሰገናል**፡፡ ዋጋውንም በመንግስተ ሰማያት ይቀበላል ማቴ 25፡21-23፣ 25፡34-40፣ 2ቆሮ 5፡10፣ ራዕ 20፡12፡፡ እዚህ ጋር ማስታወስ የሚገባው ነገር አማኙ ለሰራው መልካም ስራ ይመሰገናል እንጂ የዘላለም ሕይወት/ ደህንነት አይሰጠውም፡፡

ነገር ግን ፈሪሳውያን እንደሚያደርጉት ሰው በሥራው ሊመካ አይገባውም፤ ሉቃ 17፡10፣ 18፡-14፣ ኤፌ 2፡9፡፡ ምክንያቱም መልካም ሥራ የሰውን ክፋት ሊደመስስ አይችልም ያዕ 2፡10-11፣ ሰው ካመነም በኋላ እንኳ ክፉ ስራ ሊሰራ ይችላል፤ 1ዮሐ 1፡8፣ 2፡1፡፡ በሌላ አንጻር ደግሞ አንዳንድ አማኞች ሥራ የሌለበት እውነተኛ እምነት ይኖራል ብለው እንደሚያስቡት ማሰብ አይገባም ፤ ያዕ 2፡18-26፡፡ የሰው ሥራ በመጽደቅና በመዳን ውስጥ ምን ስፍራ እንዳለው ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 3፡20-28 (ይህም የሕግን ስራ በመስራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው)፣ ገላ 2፡16 (ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ስራ እንዳይሆን አውቀን...)፣ ኤፌ 2፡8-10 (ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና...)፣ 2ጢሞ 1፡9 (ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና..) ላይ ጽፏል፡፡

ከኃጥያት የምንድነው ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመልን ሥራ ነው፡፡ ዮሐ 19፡30፣ 6፡29፡፡ በክርስቶስ አምነን ከኃጥያት ከዳንን አዲስ ሕይወት ይኖረናል፤ 2ቆሮ 5፡17፡፡ ይህን አዲስ ህይወት እንደተቀበልን ለማሳየት መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሆኖ በእኛ በኩል መልካም ሥራ እንድንሰራ ያደርጋል፤ ገላ 5፡22-23 (የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት ራስን መግዛት ነው)፡፡ እምነታችን በመልካም ስራችን ይገለጣል፤ መልካም ስራ የእምነት ፍሬ ነው፡፡ እምነት መልካም ስራን ያስከትላል፤ ያዕ 2፡18፣ ኤፌ 2፡10፣ ማቴ 5፡16፣ 2ተሰ 2፡16-17፣ 1ጴጥ 2፡12.

**የጸጋው ብርታት፡-** ዳግመኛ የተወለዱ የእ/ር ልጆች በሙሉ የሚያውቁት አንድ እውነት አለ፡፡ ይኸውም ጸጋው አንድን ኃጥያተኛ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ ካደረገው በኋላ አስደናቂ የሆነ የሕይወት ለውጥ በዚያ ሰው ላይ የማምጣቱ እውነት ነው፡፡

የፀጋው ቀጣና ተከታታይ ሥራዎች

1. ኃጥያተኛውን ሰው ከፍርድ ያድነዋል
2. ኃጥያተኛነትንና ዓለማዊ ምኞትን ያስከደዋል
3. ጌታ እስኪገለጥ ድረስ ራስን መግዛትንና ጽድቅን እ/ርንም መምሰል ያስተምረዋል (ቲቶ 2፡11-14)

- ምንም እንኳን ደህንነታችን የሚፈጸመው በጸጋውና በእምነታችን ብቻ ቢሆንም ትክክለኛውን አማኝ ከአፍአዊ አማኝ የምንለይበት ዋነኛ መንገድ ጸጋው ሰውየውን ካዳነ በኋላ የሚሰራቸውን ሥራዎች በሰውየው ሕይወት ላይ በመፈለግ ነው፡፡
- ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጸጋ ብቻ እንደጸደቁ ካረጋገጠላቸውና ለመዳን ብለው የሕግን ሥራ ለመፈጸም እንዳይሞክሩ በታላቅ ማስጠንቀቂያ ከጻፈላቸው በኋላ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያት አይስጥ በማለት ጸጋውን ለኃጥያት መፈፀሚያ ፈቃድ እንዳያደርጉት ነግሯቸዋል፡፡ (ገላ 5፡13)
- በጸጋ የዳነ ሰው ለመታዘዝ ባርያ ይሆናል እንጂ ኃጥያት ለመስራት ባርያ አይሆንም፡፡ (ሮሜ 6፡15-19)
- ጸጋውን ለክፋት መሸፈኛ ማድረግ አይገባም፡፡ (1ጴጥ 2፡16)
- ጸጋው በእምነት ለዳነው ሰው በህይወቱ ውስጥ ኃጥያተኛነትንና ዓለማዊ ምኞትን የሚያስክድ ኃይል ስለሚሰጠው አማኙ እምነቱን በሥራ የመግለጥ ችሎታ አለው፡፡ (ቲቶ 2፡11)
- እምነት አለኝ የሚል ነገር ግን ሥራ የሌለው ሰው (አፍአዊ አማኝ) የጸጋውን ወንጌል በእምነት ለመቀበሉ ማረጋገጫ የለውም፡፡ (ያዕ 2፡14)
- ሕያው ያልሆነ የሞተ እምነት ሥራ ሊከተለው አይችልም፡፡ (ያዕ 2፡17)
- በእምነት በእ/ር ፊት የጸደቀ እምነቱን በሰው ፊት የሚገልጠው በሥራ ነው (ያዕ 2፡18)
- አጋንንታዊ እምነት በጸጋ ስለማደገፍ የሚታይ ፍሬ የለውም (ያዕ 2፡19)
- እምነት በሥራ ይፈጸማል ሁለቱም አብረው ይሄዳሉ (ያዕ 2፡21-22)
- ሥራው የመጽደቃችን ምክንያት ሳይሆን የመጽደቃችን ማረጋገጫ ነው፡፡ ይህም ማለት ሥራችን በእምነት ለመጽደቃችን ማረጋገጫ ነው፡፡ (ያዕ 2፡23)
- እምነት ፈጽሞ ያለስራ ብቻውን ተገልጦ አያውቅም (ያዕ 2፡24-26)

## ሙሉ እርግጠኝነት ሊኖረን ይችላል?

እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ሮሜ 10፡17

- የዘለለም ሕይወት **እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ** በእ/ር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ (1ዮሐ 5፡13)
- እ/ርም የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው፡፡ **ልጁ ያለው ህይወት አለው፤ የእ/ር ልጅ የሌለው ህይወት የለውም**፡፡ (1ኛዮሐ 5፡11-12)
- እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተሰፋው መንፈስ **በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤** እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፤ ለእ/ር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል፡፡ ኤፌ 1፡13-14
- እ/ር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል; የሚያጸድቅ እ/ር ከሆነ፤ የሚኮንንስ ማነው/ የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሳው በእ/ር ቀኝ ያለው፤ደግሞ ስለእኛ የሚማልደው **ክርስቶስ ኢየሱስ** ነው፡፡ (ሮሜ 8፡33-34)
- ጽድቁ፤ ቅድስናዬ እና ቤዛዬ ኢየሱስ ራሱ በመሆኑ (**1ቆሮ 1፡30**)
- የኢየሱስ ደም ዘላለማዊ መሥዋዕት በመሆኑ (**ዕብ 7፡23-27** እነርሱ እንዳይኖሩ ሞት ስለከከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፡፡ እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለእነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እ/ር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል፡፡ **ቁ.26** ቅዱስና ያለተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃግያተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባናል፡፡ እርሱም እንደነዚያ ሊቃነ ካህናት አስቀድሞ ስለራሱ ኃጥያት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጥያት እለት እለት መስዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጓልና፡፡ ሕጉ ድካም ያላቸውን ሰዎች ሊቀ ካህናት አድርጎ ይሾማልና ከሕግ በኋላ የመጣ የመሃላው ቃል ግን ለዘላለም ፍጹም የሆነውን ልጅ ይሾማል፡፡ **ዕብ 9፡12** ....አንድ ጊዜ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ..፣ **ዕብ 10፡12.** እርሱ ግን ስለ ኃጥያት አንድን መስዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእ/ር ቀኝ ተቀመጠ፡፡ **ዕብ 10፡14**. አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና፡፡
- ድነታችን በኢየሱስ ደም እንጂ በእኛ ላይ የተመሰረተ አይደለም፤ ድነታችን የሚጠበቀውም በኢየሱስ እንጂ በእኛ በራሳችን አይደለም፡፡ ዮሐ 10፡27. በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘላለም ህይወትን እሰጣቸዋለሁ ለዘላለምም አይጠፉም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም፡፡

- **ሐይማኖታዊ እንቅስቃሴዎቻችን (ቤት ክርስቲያን መሄድ፣ መጾም መጸለይ...) ሊያድኑን አይችሉም፡፡ (ዮሐ 5፡38-40:** እርሱም የላከውን እናንተ አታምኑምና በእናንተ ዘንድ የሚኖር ቃሉ የላችሁም፡፡ እናንተ በመጻህፍት የዘላለም ህይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ ነገር ግን ህይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም፡፡)
- ለደህንነት መልካም ስራ መስራት ያስፈልጋል ተብሎ በሰዎች ዘንድ መልካም የሚመስል/ ተቀባይነት የሚያስገኝ የሚመስል መልካም ስራ ቢሰራ፤ እንኳን ሊያድን ቀርቶ ይባሱኑ በእግዚአብሔር ፊት እንደ መርገም ጨርቅ ነው፡፡ (ኢሳ 64፡6. ....ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው)፡፡

## የውሃ ጥምቀት፡

ጥምቀት፡ በግሪክ "ባፕቲዞ" ሲባል የቃሉ ትርጉም ማስጠም ማለት ነው፡፡ "Baptism:- Immersion- አንድ ነገር ሙሉ uS<K< u¨<H c=gð" (c=c¨) TKf ’¨<፡፡

- ቤተ ክርሰቲያን አህዛብን ሁሉ እያስተማረች እንደታጠምቅ በጌታ ታዛለች፡፡ ማቴ 28፡19፣ ማር 16፡15
- የዘላለም ህይወት ፈጽሞ በጥምቀት አይገኝም፡፡ ሰው ለመጠመቅ የግድ በቅድሚያ በኢየሱስ በማመን መዳን ይኖርበታል፡፡

## በውኃ የመጠመቁ ትርጉም ምንድን ነው?

ሀ. ከኢየሱስ ጋር መቀበር ነው፡፡ ሮሜ 6፡4፣ ቆላ 2፡12. አማኙ ከጌታ ኢየሱስ ጋር አብሮ ለመቀበር እንኳን ተስማማ (የተባበረ) መሆኑን ይገልጽበታል፡፡ ይህም ከውሃው ከሚጠልቅበት ቅጽበት ይገለጣል፡፡

ለ. ከኢየሱስ ትንሳዔ ጋር መተባበሩን ያሳል፡፡ ሮሜ 6፡4-5. ይህም ከውኃው በሚወጣበት ቅጽበት ይገለጻል፡፡

ሐ. ከዚያ በኋላ በአዲስ ሕይወት መመላለስ ይገባል፡፡ ሮሜ 6፡7-11

ከጌታ ኢየሱስ ጥምቀት መማር ማቴ 3፡1-17

እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ሮሜ 10፡17

- ✓ ዮሐንስ የንሰሃ ጥምቀት ያጠምቅ ነበር፡፡ ማቴ 3፡11
- ✓ ሰዎች ሁሉ ኃጥያታቸውን እየተናዘዙ ጠመቁ ነበር ማቴ 3፡5
- ✓ ያን ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ሊጠመቅ ከገሊላ- ዮርዳኖስ መጣ

**<u>አስታውስ/ሽ/</u>፡-** ጌታ ኢየሱስ ፈጽሞ ኃጥያት አያውቅም፡፡

- ነገር ግን ኃጥያተኞች የሚጠመቁትን ጥምቀት ሊጠመቅ መጣ፡፡ ማቴ 3፡13
- ዮሐንስም ይከለክለው ጀመር፣ ዮሐንስ ትክክል ነበር ምክንያቱም ኢየሱስ ኃጥያት የለበትምና፡፡
- ለኢየሱስ ቢጠመቅ የሚጨምርለት፣ ባይጠመቅ የሚጎድልበት ነገር አልነበረም
- ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ አጥጋቢ ምክንያት ነበረው፡፡

**"እንግዲህ ፍቀድልኝ፣ ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባናልና አለው" ማቴ 3፡15**

**<u>አስታውስ/ሽ/</u>** ደህንነት ወይም የዘላለም ሕይወት የሚገኘው በጌታ ኢየሱስ ለኃጥያታችን መሞትና መነሳት እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በማመን ብቻ ነው፡፡

- ሰው አምኖ ከዳነ በኋላ ጊዜ ካለው ግን የውሃ ጥምቀት በመውሰድ ከጌታ ጋር በመቃብር እንኳን ለመተባበር ፈቃደኛ መሆኑን ማሳየት ይኖርበታል፡፡

## <u>እነማን ይጠመቁ?</u>

- አንድ ሰው የውሃ ጥምቀትን ከመውሰዱ በፊት ሊያሟላቸው የሚያስፈልጉ ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች አሉ፡፡1. የወንጌል ትምህርት 2. እምነት 3. ንሰሐ/መናዘዝ
- ሐዋርያት እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ያላሟሉ ሰዎችን አያጠምቁም ነበር

  **ለምሳሌ** 1. ጴጥሮስ ሐዋ 2፡14-47

  1. ጰየጥሮስ ወንጌልን ሰበከ ሐዋ 2፡14-36
  2. ሰዎቹ ልባቸው ተነካ (አመኑ) ሐዋ 2፡37
  3. ንሰሃ እንዲገቡ ታዘዙ ሐዋ 2፡38
  4. ተጠመቁ ሐዋ 2፡41

**<u>አስታውስ/ሽ/</u>**፡- ቃሉን የተቀበሉት ብቻ ተጠመቁ ሐዋ 2፡41

ሕጻናት ወንጌል አይሰበከላቸውም እነርሱም፣ ተረድተውት ልባቸው አይነካም፣ እንዲሁም ንሰሃ ግቡ የሚባሉበት ሁኔታ የለም፡፡

**ለምሳሌ** 2. ዲያቆን ፊሊጶስ ሐዋ 8፡26-40

1. ስለ ኢየሱስ ወንጌል ሰበከለት ቁ. 35
2. ሰውየው ለመጠመቅ እንኳ ዝግጁ ሆነ ቁ. 36፡፡ ፊሊጶስ ግን መጠመቅ ትችላለህ አላለውም፡፡ ይልቅስ በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል አለው፡፡
3. ተናዘዘ ቁ. 38
4. ተጠመቀ ቁ. 38-39

- ✓ በአጠቃላይ ጥምቀት አማኙ ኢየሱስን በማመን ብቻ የዘላለም ሕይወት ተስፋ ከተቀበለ በኋላ የቤተክርስቲያን/የአጥቢያ/ አባል ለመሆንና እንደሌሎች ወንድሞቹ ሁሉ ለኃጥያት መሞቱንና ከጌታ ኢየሱስ ጋር መቀበሩን፣ መነሳቱን እንዲሁም በአዲስ ሕይወት ለመመላለስ መወሰኑን የሚያሳበት ነው፡፡
- ✓ ጥምቀት ለደህንነት ያስፈልጋል ብሎ ማመን የክርስቶስን መስቀል ከንቱ ማድረግ ነው፡፡ 1ቆሮ 1፡17 (ለማጥመቅ ክርስቶስ አላከኝምና ወንጌልን ልሰብክ እንጂ የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን በቃል ጥበብ አይደለም፡፡

እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ሮሜ 10፡17

## የጌታ እራት፡

“….ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመሰገነ ቆርሶም፡- እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፣ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፡፡ እንደዚሁም ከ እራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንስቶ ይህ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፡፡ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፡፡ 1ቆሮ 11፡23-26”

ጌታ ኢየሱስ በእርሱ አምነው ለዳኑት አማኞች ሁሉ ከጥምቀት ቀጥሎ ይፈጽሙት ዘንድ በቋሚነት ከሰጣቸው ሥርዓቶች ሁለተኛው ነው፡፡ የጌታ እራት ለሁሉም አማኞች የጌታን ሞት ያስቡበት ዘነድ ተሰጠ ቅዱስና ክቡር ሥርዓት ነው፡፡

### የጌታ እራት ስያሜዎች

1. የጌታ እራት 1ቆሮ 11፡20
2. የጌታ ማዕድ 1ቆሮ 10፡21
3. እንጀራውን መቁረስ ሐዋ 2፡42

### ዓላማው፡-

1. **የጌታ ሥጋና በደሙ የተፈጸመው የአዲስ ኪዳን መታሰቢያ**

ጌታ ኢየሱስ ይህንን ሥርዓት አሳልፎ ከሰጠበት ሌሊት ጀምሮ እርሱ እስኪመጣ ድረስ የጌታን ሞት የምናስብበትና በእንጨት ላይ የዋለ ሥጋውንና የፈሰሰውን የሚያነጻ ደሙን የምናስታውስበት መታሰቢያ ነው፡፡

ይህ ማለት ቂጣው አሁን በአብ ቀኝ ያለውን እውነተኛ ሥጋውን ያስታውሰናል እንጂ ራሱ ቂጣው ሥጋ ነው ወይም ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ እንዲሁም ጽዋው ለዓለም ኃጥያት የፈሰሰውን ደሙን ያስታውሰናል እንጂ በራሱ የወይን ጠጁ ደም ነው ወይም ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ ቂጣውንና የወይን ጠጁን ተለውጦ ሥጋ እና ደም ይሆናል ማለት እጅግ የተሳሳተ መረዳት ሲሆን በአብ ቀኝ የተቀመጠውን ያን ክቡር ኢየሱስ ማክፋፋት ነው፡፡ እርሱ ሁልጊዜ ይሰዋል እንደማለት ነው፡፡ ዕብ 9፡26፡፡

ምሳሌያዊ ማብራሪያ፡- ለምሳሌ አንድ ወንድማችን ፎቶግራፉን ቢሰጠንና ይህ እኔ ነኝ ህን ለማስታወሻ ውሰዱት ቢለን ፎቶግራፉ በራሱ ግን ልጁ ራሱ አለመሆኑን እናውቃለን፡፡ ነገርግን ለወንድማችን ባለን አክብሮትና ፍቅር መጠን ለፎቶግራፉ ያለን ክብር ይወሰናል፡፡

2. **የጌታን መከራና ሞት ማስታወሻ**

“ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት ሉቃ 22፡20”፡፡ በዚህም መሰረት ቤተክርስቲያን ቂጣ/እንጀራ እና የወይን ጠጅ በማዘጋጀት የጌታን መከራና ሞት በማሰብ በዚህም ለእርሷ ተደረገላትን መዳን እያሰበች ጌታን ታመሰግንበታለች፡፡ እንጀራውንም በመብላት ጽዋውንም በመጠጣት የጌታን ሞት እርሱ እስኪመጣ ድረስ ትናገራለች፡፡ 1ቆሮ 11፡26

3. **የቤተክርስቲያን አንድነት መግለጫ**

አንድ እንጀራ ስለሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋነን ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና 1ቆሮ 10፡17፡፡ እግዚአብሔርና ቃሉ የሚያውቁት አንዲት ቤተክርስቲን እንዳለች ብቻ ነው፡፡ በጌታ ኢየሱስ ያመኑና የዳኑ በሙሉ አንድ ላይ አንዲት ቤተክርስቲያን ተብለው ይጠራሉ፡፡ አማኞች በቁጥር ብዙ ቢሆኑም ስንኳ ነገር ግን አንድ አካል/ቤተክርስቲያን/ ናቸው፡፡ ይህን የሚገልጹትም በአካል ምንም ብዙዎች ቢመስሉም ግን አንድ ስጋ መሆናቸውን አንዱን ቂጣ/እንጀራ በመቁረስ ያረጋግጣሉ፡፡ 1ቆሮ 12፡12-28

እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ሮሜ 10፡17

## እንማን ይካፈሉ፣ ይቁረሱ?

የጌታ እራት ሥርዓት የተሰጠው አምነው ለዳኑ አማኞች በሙሉ ሲሆን ክርስቲያኖች ሁሉ ጌታን እንዲያስቡበት ጌታ አጥብቆ ይፈልጋል፡፡ ይህ ማለት ግን አማኞች ለመታሰቢያው ያላቸው ክብር ዝቅ እንዳይል ሊጠነቀቁ ይገባቸዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ አማኞች እንጀራው እንዳይቆርሱ ሊያግዷቸው የሚችሉ ነገሮች መኖራቸውን ማወቅ ጠቃሚ ነው፡፡

## ማስታወሻ

የጥምቀትም ይሁን የጌታ እራት ሥርዓቶች **ለመዳን የተሰጡ ሳይሆኑ ለዳነ ሰው ብቻ የተሰጡ ሥርዓቶች ናቸው**፡፡ ከዘላለም ሕይወት/መዳን/ ጋር ፈጽሞ ግንኙነት የላቸውም፡፡

- **መካከለኛ፡** በእግዚአብሔር ፊት ለበደለኞች የሚያማልድና ከእግዚአብሔር ምህረትን የሚያስገኝ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ካህናትና ነቢያት እንዲሁም ሙሴ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የመካከለኛነት ስራ ይሰሩ ነበር፡፡ ዘዳ 18፡18-21፣ ዘሌ 9፡7፣ ዕብ 5፡14፡፡ **ኢየሱስ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው**፡፡ ዮሐ 1፡17፣ ዕብ 7፡27-28፣ ዕብ 8፡6፣ ዕብ 9፣ ዕብ 15፡23-24፣ ዕብ 10፡1፣ 12፡24፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የካህናትን፣ የነቢያትንና የሙሴን መካከለኛነት በመፈጸሙ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለ መካከለኛ እርሱ ብቻ ነው፡፡1ጢሞ 2፡5 (አንድ እግዚአብሔር አለና፣ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው)፡፡
- **ካህን፡** በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሆኖ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ፡፡ ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን ካህን ነው፡፡ ዕብ 5፡5-6፣ 7፡11-28፡፡ ካህን በተለይ ሁለት ነገሮችን ይሰራል፡፡

1. ***መሥዋዕትን ያቀርባል፡፡*** ኢየሱስም ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ራሱን አቀረበ፡፡ ይህንንም በማድረጉ ስለ ኃጥያት ይደረግ የነበረውን የብሉይ ኪዳንን ሥርዓት ፈጸመ፡፡ ለሚያምኑበትም የመዳን መንገድን ከፈተ፡፡ በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር በግ ተብሏል፡፡ዮሐ 1፡29፡፡ በኢየሱስ ሞት የእግዚአብሔር ጽድቅና ፍቅር ተገልጧል ሮሜ 3፡26፣ 5፡8፡፡ በአጠቃላይ ኢየሱስ በኃጥያተኞች ፈንታ ሞተ፣ በሞቱም ኃጥያታቸው ይደመሰሳል፤ ኢሳ 53፡5፣ ማር 10፡45፣ ሮሜ 5፡15፣ 1ጴጥ 2፡24፣ 3፡18፣ ራዕ 1፡4-5፡፡

2. **ካህን ለሕዝቡ ይጸልያል፤ በእር/ም ፊት ይገኝላቸዋል፡፡** ኢየሱስም በምድር ሳለ ለተከታዮቹ ማለደ (ሉቃ 22፡32፣ ዮሐ 17፡6-26)፤ አሁንም አዳኝ ሆኖ በእግዚአብሔር ቀኝ ለእነርሱ ይገኛል (ሮሜ 8፡34፣ ዕብ 7፡23-25፣ 1ዮሐ 2፡1-2

❖ **ማለደ**፡ 1. ጧት ተነሣ ማቴ 20፡21፣ ሉቃ 21፡28. 2. አንዱ ስለ ሌላው ለመነ ሮሜ 8፡26-34

**ምልጃ, አማለደ፡** አንዱ ስለ ሌላው መለመንን ያሳያል፡፡

- እነ ሙሴ በምድር ላይ ሳሉ ስለ እስራኤል ማለዱ፤ ጸሎታቸውም ተሰማ፡፡ ዘኍ 14፡19-20፣
- ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ለመነ ሉቃ 22፡32፣ ዕብ 5፡7-10፣
- ምእመናን ለሌሎች እንዲለምኑ ታዝዘዋል ፊል 4፡6፣ 1ጢሞ 2፡1-2.
- መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ለአማኝ ያማልዳል፤ ይህም ለድካማቸው ኃይልን ይሰጣል ማለት ነው፡፡ ሮሜ 8፡26፡፡

ክርስቶስ "… ስለ እነርሱም **ሊያማልድ** ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል፡፡ ዕብ 7፡25"

የኢየሱስ ምልጃ ግን እንደ ሰው ልመና አይደለም፡፡ ምክንያቱም፡-

1. አንድ ጊዜ ራሱን መስዋዕት አድርጎ በማቅረቡ ለአማኝ ፍጹም ደህንነት አስገኝቶላቸዋል፡፡ (ዕብ 10፡14 አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና፡፡)

2. ለዘላለም ህያው ሆኖ በሰማይና በምድር ሥልጣንን ሁሉ በመቀበል በአብ ቀኝ ተቀምጧል፡፡ ሮሜ 8፡34፣ ዕብ 7፡25፣ 1ዮሐ 2፡1(**ማንም ኃጥያትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው**)፡፡